# ሲሾቅ ፤ ቂሉ ማሞ

ጅቡ ሄደ ስንል ፤ ተወረን ባሳማ
እንኳን ሊነጋጋ ፤ ሰው ውጦት ጨለማ
ንብረትና ሃብቱን ፤ ያለግባብ ሲቀማ
ህዝብ እያለቀሰ ፤ ጩኸት እያሰማ
ወገን ሲፈናቀል ፤ ከሸገር ከተማ
አብይና ለማ ፤ አገር እያገማ
ያጨበጨብንለት ፤ አቢቹ መች ሰማ?
ይሳለቅብናል ፤ ቁጭ ብሎ ከማማ ።

ህዝብ እያለቀሰ ፤ ቢያሰማም እሮሮ
ማየት የተሳነው ፤ ከቃላት አሻግሮ
ልቡን ሰውሮበት ፤ ውብ ቃላት ተናግሮ
በአቢቹ ፍቅር ፤ አገር ምድር ሰክሮ
አብይን ለሚተች ፤ መች ይሰጣል ጆሮ
ያጠቃል ተቺውን ፤ ከተቻለው ዞሮ
ከእንቅልፉ የሚነቃው ፤ ዘመን አስቆጥሮ ።

እየተመረጠ ፤ የትውልድ ሃረጉ
አማራው ሲዋረድ ፤ ክብርና ማረጉ
ደመቀና ገዱ ፤ እያደገደጉ
ለውጥ መጣ እያሉ ፤ ህዝብ እያዘናጉ
ከመላው ኢትዮጵያ ፤ እየጠራረጉ
የምናየው ዛሬ ፤ አማራን ሲያስወጉ
አይገባኝም ለኔ ፤ ሃቁን መሸሸጉ ።

ልክ እንደ ቀደመው ፤ ዛሬም ባደባባይ
በምርኮኛ ቡድን ፤ በወያኔ አገልጋይ
ቀና ብሎ ቢያይም ፤ ጥቁር ሆኖ ሰማይ
እንደ ገና ዳቦ ፤ ከታችና ከላይ
እሳት ሲነድበት ፤ አማራው ምድር ላይ
ምን ጋረደው አይንህ ፤ እውነቱን እንዳታይ?
በድን ያደረገህ ፤ ግዑዝ እንደ ድንጋይ?
ማዕድ ትቆርሳለህ ፤ ከወንድምህ ገዳይ ።

ምሁሩም አድር ባይ ፤ ላበላው አዳሪ
እጅጉን የሚወድ ፤ መሸታና አዝማሪ
ተሚጋች እንዳይሆን ፤ እሱ ሆኖ መሪ
የማይመኩበት ፤ የሆነ አሳፋሪ
እሱን የሚገደው ፤ ያየው ፍርፋሪ
መቼ ጆሮ ሰጠና ፤ ለወገኑ ጥሪ ።

በትግል አጋር ስም ፤ በሃሰት አስታሞ
ለእርድ እያዘጋጀው ፤ ለመጪው ለከርሞ
አማራው ወገኔ ፤ ሲያንቀላፋ ቆሞ
ከሰሜን በትግሬ ፤ ከደቡብ ኦሮሞ
ይታየኛል ለኔ ፤ ሲሾቅ ቂሉ ማሞ
እሳት ሲያነዱበት ፤ ትግሉ ተፋፍሞ ።

ታዛቢው

February 20, 2019